# ዓምደኛ ወይስ የተቃዋሚ ፓርቲ አባል?

ናትናኤል አበራ

ዴሞክራሲንና የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታን በተመለከተ ጥቂት ነገሮችን ማንሳት ጉዳዩን በደንብ ግልጽ ለማድረግ ሳያግዘኝ አይቀርም፡፡ ዴሞክራሲ ስለፈለጉትና በፈለጉት መንገድ የሚገነባ አይደለም፡፡ ቢያንስ በሀገሩ ባህላዊና ታሪካዊ ሁኔታዎች ይወሰናል፡፡ ለዚህም ነው የየሀገሩ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ተለያይቶ የሚገኘው፡፡ በልጽገዋል የሚባሉት ሀገራትም ቢሆኑ ቢያንስ መሠረታዊ በሚባሉት የዴሞክራሲ ሥርዓት መገለጫ ጉዳዮች ላይ (እንደ የህግ የበላይነት፣ የምርጫና የመሳሰሉት) ተመሳሳይነት ቢኖራቸውም በብዙ መንገዶች ከየሀገራቸው ባህላዊና ታሪካዊ ሁኔታዎች ጋር ተያዞ በመጣ ምክንያት የዴሞክራሲያዊ ሥርዓታቸው ግንባታ የተለያየ ነው፡፡

የአፍሪካን ዴሞክራሲ ከተመለከትን ደግሞ አብዛኛው ጫና ያረፈበትና የውጭ ጣልቃ ገብነት የሚፈቅድ እንደነበር የታሪክ ድርሳናት የከተቡት ጉዳይ ነው፡፡ በ1973 እ.ኤ.አ. የተከሰተውን ዓለም አቀፍ የነዳጅ ቀውስ ተከትሎ አፍሪካውያን እዳ መክፈል ሲሳናቸው በቀጥታ መንግሥታዊ ሥርዓታቸውን ለአይ ኤም ኤፍ እና የዓለም ባንክ አሳልፈው ለመስጠት ተገደዋል፡፡ እዳው በ1980ዎቹ እየተባባሰ ሲመጣ የአፍሪካን ኢኮኖሚ እንዲመሩ በሚል ከአበዳሪዎቹ ውክልና የተሰጠው መንግሥታዊ ላልሆኑ ድርጅቶች ነው፡፡ እነዚህ በአይ ኤም ኤፍ እና የዓለም ባንክ ውክልና አፍሪካ የገቡት መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ግን ሥራቸው ኢኮኖሚ ሳይሆን በየሀገራቱ የፖለቲካ አስተዳደር ሥርዓት ውስጥ ጣልቃ በመግባት የሚፈልጉትን ዓይነት የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መጫን ነው፡፡ በነገራችን ላይ እነዚህ ኃይሎች ምርጫ እስከማካሄድ የሚዘልቅ ሚናም ነበራቸው፡፡ በመሠረቱ ለብዙ አፍሪካውያን ሀገራት የውጭ ተጽዕኖ መጋለጥና ስማዊ ዴሞክራሲ ማበብ መነሻ ምክንያቱ የየሀገራቱ የኢኮኖሚ መሠረቱ ኪራይ ሰብሳቢነት መሆኑ ነው፡፡ በእነዚህ ሀገሮች ሥልጣን የመያዝ ጉዳይ የመበልፀግ ጉዳይ ስለሆነ ምርጫዎች የሚጠናቀቁት በግጭት ነው፡፡ ዳኞቹ ደግሞ ምዕራባውያን ወይም የኒዮ ሊበራል አቀንቃኞች ናቸው፡፡

በግጭት የተጠናቀቀውንና የቅርብ ጊዜ ክስተት የሆነውን የኮትዲቭዋር ምርጫ ፈረንሣዮች መዳኘታቸውን ልብ ይሏል፡፡ ለአፍሪካ የዴሞክራሲ ተምሣሌት ነች የሚሏት ጋናም ብትሆን ዴሞክራሲዋ ስማዊ ነው፡፡ የተገነባው በነዳጅ ሀብት የኪራይ ሰብሳቢነት ፖለቲካል

ኢኮኖሚ ላይ በመሆኑ፡፡ የመካከለኛው ምሥራቅ ሀገራትን ብንመለከትም ያው በተመሳሳይ ከኪራይ ሰብሳቢነት ፖለቲካል ኢኮኖሚ ላይ የተገነባ ዴሞክራሲ በመሆኑ ነው አሁን ለመነቃነቅ የበቃው፡፡

እዚህ ላይ ዴሞክራሲ ከመበልጸግና ካለመበልጸግ ጋር ተያይዞ የሚገነባ ነው የሚል የተሳሳተ ድምዳሜ መያዝ የለበትም፡፡ ያለዴሞክራሲ የበለጸጉትን እነ ኖርዌይ፣ ስዊዲን እና ጃፓንን ማስታወስ ያስፈልጋል፡፡ ጀርመን በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወቅት የተደራጀችና የበለጸገች ሀገር እንደነበረች እናስታውሳለን፡፡ ነገር ግን የበለጸገው ሀገሯና ሕዝቦቿ ፋሽቶቸችና ፀረ ዴሞክራቲክ ኃይሎች እንደነበሩም መታሰብ አለበት፡፡

በነፈሰ ቁጥር የማይወዛወዝ ዴሞክራሲ በልማታዊ መሠረት ላይ እና በሀገሬው ነዋሪ ላይ የተገነባ ዴሞክራሲ ነው፡፡ በዚህ ረገድ ሊጠቀስ የሚችለው የኢትዮጵያ ዴሞክራሲ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲ ሀገር በቀል ነው፡፡ የተገነባው የሀገሬውን ሕዝብና ብሄር ብሄረሰቦችን መሠረት አድርጎ ነው፡፡ ልማታዊ መንግሥት ልማታዊ የእድገት አቅጣጫን መሠረት አድርጎ የተገነባ ዴሞክራሲ ነው፡፡ ቢያንስ ዛሬ በሀገራችን የትኛውንም ዓይነት ርዕዮት የሚከተል መንግሥት ቢመሰረት ሕዝቡን ሊነጥቅ የማይችላቸው መብቶች አሉ፡፡ ራስን በራስ የማስተዳደርና የብሄር እኩልነት መብቶች በልማታዊ መሠረት ላይ በልጽገዋል፡፡ እነዚህን መብቶች የማይቀበል መንግሠት በኢትዮጵያ ቦታ ሊኖረው እንደማይችል አሁን እርግጥ ሆኗል፡፡

በኢትዮጵያ እየተገነባ ያለው ዴሞክራሲ አንድ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ማኅበረሰብ ለመፍጠር የሚያስችል እንደሆነ በተጨባጭ እየታየ ነው፡፡ ዛሬ በኢትዮጵያ እያንዳንዱ ብሄረሰብ የራሱን ነፃነት እያሰፋ ለጋራ አንድነት የሚሰጠውንም ትርጉም በዚያው ልክ እያሰፋ መጥቷል፡፡ በዚህም የተነሳ ከባድ በሆነው የውድድር መድረክ /Globalization/ በመሳተፍ አንድ የኢኮኖሚ ማኀረሰብ በመፍጠር ሂደት ላይ ነው፡፡

ማኅበረሰቡ በአንድ ህገ መንግሥት እየተመራ ነው፡፡ አንድ ሲቪል ሰርቪስ ካለው ፖለቲካዊ ውሣኔ የሚሹ ጉዳዮችን እንደ መከላከያ፣ የውጭ ጉዳይና ገንዘብ የማተም የመሳሰሉትን የፌዴራል መንግሥት እንዲያስተዳድር ሕዝቡ ፈቅዷል፡፡ ይህ ደግሞ አንድ የፖለቲካ ማኅበረሰብ መፍጠር እንደሚቻል የሚያመላክት ነው፡፡ በተቃራኒ ለቆመው

ኃይል ፀረ ዴሞክራቲክ የመንግሥት መገለጫ ሲል የሚያብጠለጥለውን ጉዳዮች ስናይ መጀመሪያ የምናገኘው የነባር ሥርዓቱን ነው፡፡

የመንግሥት ሠራተኛውን ደመወዝ ከማሻሻል ጀምሮ የሀገሪቱን ልማት ለማፋጠን ታክስ መሠረታዊ ጉዳይ ነው፡፡ ታክስ መክፈል በመሠረቱ ትክክለኛ ዴሞክራሲ /Real Democracy/ መሠረታዊና ዋና ባህሪ ነው፡፡ ፍትሃዊ የሆነ የሀብት ክፍፍል የሚኖረው ሁሉም ባተረፈው ልክ ታክስ መክፈል ሲችል ነው፡፡ አሁን ያለው ልማታችን ዘላቂነት የሚኖረው ታክስ መክፈል ስንችል እንጂ በነ አሜሪካና ቻይና ብድር አይደለም፡፡

መሬትን የተመለከተው ደግሞ ሁለተኛ ነው፡፡ መሬት የግል በሆነበት ሁኔታ መንግሥት ካሳ እየከፈለ መሠረተ ልማት መገንባት የሚችል አይመስለኝም፡፡ መንግሥት ማንኛውም ዜጋ በጉልበቱ ለሰራው ቤትና ላፈራው ሀብት ተገቢውን አክብሮት መስጠት ይገባዋል፡፡ አንድ በቅርብ ጊዜ የተደረገ ጥናት እንዳመለከተው ቦሌ አካባቢ አንድ ሺህ ካሬ ሜትር 24 ሚሊዮን ብር ነው፡፡ በደቡብ አፍሪካ ጁሃንስበርግ ደግሞ ተመሣሣይ የሆነ ካሬ ሜትር ቦታ አምስት ሚሊዮን ብር ነው፡፡ ይህ የሚያመለክተን በደቡብ አፍሪካ የሚገኙት ባለሃብቶች /ግለሰቦች/ መሬት የሚገዙት ለማልማት እንደሆነና በእኛ ሀገር ቦሌ ግን መሬት ገዥ አጥሮ ለመሸጥና በአቋራጭ ለመበልጸግ ነው፡፡ ስለሆነም ሥርዓት ያጣውን የመሬት አስተዳደር ማስተካከል ተገቢ ነበር ብሎ መውሰድ ይቻላል፡፡ ነገር ግን በእኛም ሀገር ቢሆን እንዲህ እንደምናወራው መንገዱ ሁሉ ጥርጊያ ነው ማለት አይቻልም፡፡ ከውስጥ ችግራችን ባሻገር በራሳችን ኃይሎች የሚታገዙት የውጭ ኃይሎች ጫና አሁንም ከባድ ነው፡፡

የኒዮ ሊብራሉን ጎራ ጫና እዚህ ጋር መመልከቱ የዴሞክራሲ ሥርዓታችንን ግንባታ ከውስጥ እስኪረጭ የዘለቀ ፈተና መገንዘብ ያስችለናል፡፡ ኢህአዴግ አገሪቱን በተረከበ ማግስት ጀምሮ በኒዮ ሊበራል ኃይሉ ሲደርስብን የነበረው ጫና የኢኮኖሚ ነው፡፡ መሬት መሸጥ መለወጥ አለበት፣ ትልልቅ የመንግሥት ተቋማት (ቴሌ፣ ባንክ፣ ንግድ መርከብ፣ የኤሌክትሪክ ኮርፖሬሽንና የመሳሰሉት) ወደግል መዞዋወር አለባቸው፣ መንግሥት የወለድ ምጣኔና የውጭ ምንዛሬን መተመን የለበትም የሚሉና የመሳሰሉት ጫናዎች ለበርካታ ዓመታት የዘለቁ ሲሆን ካለፉት አራት ዓመታት ወዲህ ይህ የኢኮኖሚ ጫና የረገበው በሀገሬው ህዝብ ላይ የተገነባው ዴሞክራሲና ልማታዊ መስመር ስኬታማ ሆኖ በመገኘቱ ነው፡፡ አሁን ወቀሳው የፖለቲካ ሆኗል፡፡

በሰብዓዊ መብት ሽፋን በመንደር የማሰባሰቡ የልማት አቅጣጫ እየተወገዘ ነው፡፡ ኢትዮጵያ እየለማች መሆኑን የሚቀበሉት እነዚህ ኃይሎች ሀገሪቱ የለማችው በፀረ ዴሞክራሲያዊ መንገድ ነው እያሉ ነው፡፡ (development without democracy) የሚል ስያሜ በመስጠት፡፡

መልካም አስተዳደርን በተመለከተ በሀገራችን እንደ አጠቃላይ ወደፊት የመሄድ ሁኔታ ይታያል፡፡ ግን የመዋዠቅና ወደኋላ የመመለስ ሁኔታም መኖሩ የማይታበል እውነታ ነው፡፡ መንግሥት ለልማቱም ሆነ ለመልካም አስተዳደር ሥራዎች እኩል ሚዛን ካልሰጠና አንዱን ከዘነጋ ከቁጥጥር ውጪ የመሆን አዝማሚያና የሕዝብ ምሬት መከሰቱ አይቀርም፡፡ ስለሆነም ይመስላል ካለፉት ሁለት ዓመታት ጀምሮ ሚዛን የመጠበቅ ተግባራት እያየን ያለነው፡፡

ሰፋፊ የልማት ሥራዎች በሀገራችን መኖራቸው በራሱ በመልካም አስተዳደር ጉዳዮች ላይ ችግር የሚፈጥር እንደሆነም መዘንጋት የለበትም፡፡ እነዚህ ሥራዎች በርካታ ዜጎችን ከታች ወደ ላይ የሚመጡት ግለሰቦች ደግሞ ሳይዘጋጁ የሚመጡ ከሆነ አስተዳደሩ መበላሸቱ አይቀርም፡፡ ያም ሆኖ ግን መልካም አስተዳደር በመንግሥት የሚሰጥ ስጦታ አለመሆኑ መታወቅ አለበት፡፡ ከመሠረቱ በኅብረተሰቡ የነቃ ተሳትፎና ትግል የሚረጋገጥ ጉዳይ ነው መልካም አስተዳደር፡፡ ለመልካም አስተዳደር እውን መሆን ሰፊና ጥልቅ ተሳትፎ ያስፈልጋል፡፡ ሕዝብ ወደ ኋላ ከተመለሰ የአመራሩ እድል እየሰፋ መንገዱ ይጠባል፡፡ ይህም ሆኖ መልካም አስተዳደር በማረጋገጥ ጉዳይ ፍጹም መሆን አይቻልም፡፡ ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓትም ሆነ ለነጻ ገበያ ሥርዓት ጀማሪዎች መሆናችንም ሊጤን ይገባዋል፡፡ እየተማርን ነው መሄድ የምንችለው፡፡

እዚህ ጋ ነው እንግዲህ ከሞላ ጎደል በሚባል ደረጃ የሀገራችን ተቃዋሚ ፓርቲዎችና የግሉ ፕሬሶች የሚመጡት፡፡ እነዚህ ኃይሎች ሁሉን ታገኛለህ ወይ ሁሉን ታጣለህ መርህ ከኒዮሊበራል ኃይሎች ጋር እየሰሩ ቢሆንም ሁለቱም በየፈርጃቸው ነጻ መሆናቸውን ግን ከመናገር ተቆጥበው አያውቁም፡፡ ተቃዋሚው በየስብሰባውና ኤምባሲው ምህዳር ጠበበ፣ የተወካዮች ምክር ቤት ወንበር እነሰን፣ ህገ መንግሥቱ ተጣሰ፣ የህግ የበላይነት የለም ሲሉ በአንድ ቃልና ቋንቋ ያስተጋባሉ፡፡

አንድ ላይ ነው የምትሰሩት ሚናችሁን ለዩ ሲባሉ ነጻና ገለልተኛ መሆናቸውንና ስለሀገራቸው ለየብቻ እየሰሩ መሆኑን ይገልጻሉ፡፡ በተመሳሳይ ቀንና ሰዓት ተመሳሳይ መግለጫ ያወጣሉ፣ ይጽፋሉ፡፡ ለገዥው ፓርቲ መልካም ሥራ ሁለቱም እውቅና አይሰጡም ንፉግ ናቸው፡፡ በህገ መንግሥቱ ላይ በጥልቅና በነጠላ አንቀጾችም ላይ ያላቸው አቋምና ማብራሪያ ተመሳሳይ ነው፡፡ ኒዮ ሊበራሉም ህገ መንግሥት ለመለወጥ ወይም መንግሥት ለመገልበጥ አብሯቸው በመስራት ላይ ነው፡፡ በምርጫ 97ቱ የነበረውን የአውሮፓ ህብረት ያስታውሷል፡፡ አሁን ደግሞ ሂውማን ራይትስ ዎች የጋምቤላ ክልል ኢንቨስትመንትና መንደር ማሰባሰብ ከሰብዓዊ መብት ጥሰት እስከ "ሩዝ የተቅማጥ መድኃኒትነት" በዘለቀ ፕሮፖጋንዳ ተራምደዋል፡፡ ግን እነዚህ ኃይሎች የተለያዩ ቢመስሉም የአንድ ሣንቲም ሁለት ገጽታዎች ናቸው፡፡ ሰበካቸው ፍልሚያቸው ትግላቸው ሁሉ የጨኸትና የፀረ ዴሞክራቲክ መንገድ ነው፡፡ የማያምኑበትን ህገ መንግሥት ከአጀንዳው ጋር ከተስተካከለ ህገ መንግሥቱ ይከበር ሲሉ ስለህግ የበላይነት ሊሰብኩ ይሞክራሉ፡፡ ከአጀንዳቸው ጋር እስካልተጣጣመ ደግሞ ‹‹ህገ አራዊት›› ሲሉ ህገ መንግሥቱ ላይ ያፌዛሉ፡፡ የእነዚህን ኃይሎች የአንድ ሣንቲም ሁለት ገጽታ ከአዲስ አድማስ የየካቲት 3 ቀን 2004 ዓ.ም እትም ማረጋገጥ ተችሎኛል፡፡

በአራት ንዑሳን ርዕሶች በማጀብ ‹‹ተቃዋሚ ፓርቲ ሥልጣን ይይዛል ብዬ አስባለሁ›› በሚል ርዕስ የአንድነት ፓርቲ ምክትል ሊቀ መንበርና የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባል የሆኑትን የተከበሩ አቶ ግርማ ሰይፉ በፊት ገጹ ይዞ የወጣው አዲስ አድማስ ጋዜጣ ካቀረበላቸው ጥያቄዎች መካከል ሁለቱ የተቃዋሚ ፓርቲዎች ነጻ አምደኞች ነን የሚሉ ጸሀፊዎችን እንዲሁም ፕሬሱን ለመጠርጠር ምክንያት ሆነውኛል፡፡

የፓርላማ አባላት በእርስዎ አስተያየት ወይም ለእርስዎ በሚሰነዘር መልስ በተደጋጋሚ ይስቃሉ... የሚለው ጥያቄና የአንድነት አመራሮች መግለጫ ስትሰጡ በአንድ ዓይነት አባባል ነው እንደዩኒፎርም፡፡ አንዳንዶቹ ከእንግሊዝ ሌበር ፓርቲ የተኮረጀ ነው ይላሉ፡፡ የሚለው ሁለተኛ ጥያቄ ቀልቤን ገዝተውኛል፡፡ እነዚህን ጥያቄዎች አቶ ግርማ እንደሚከተለው መልሰዋል፡፡

‹‹በእኔ ጥያቄ አይመስለኝም የሚስቁት ሆኖም ጠቅላይ ሚኒስትሩ በየስድስት ወሩ አንዴ እየመጡ ቢያስቋቸው ምንም ክፋት የለውም፡፡ የተመረጡት ለመሳቅ ከሆነ እነሱ ናቸው

የሚያውቁት፡፡ እኔ እንደምታዩኝ ቂጭ ብዬ የተመረጥኩበትን ዓላማ ሰርቼ ነው የምወጣው፡፡›› ለመጀመሪያው ጥያቄ የሰጡት ምላሽ ነበር፡፡

## ኤሊያስ ሰ እና የተከበሩ አቶ ግርማ ሰይፉ- አቤት ሲያገጣጥም!!

‹... ከእንግሊዝ ሌበር ፓርቲ የተላከው አጋጣሚ ይሆናል እንጂ አስበን ያደረግነው አይደለም፡፡ እኛ መኮረጅ አንፈራም አሪፍ ከሆነ ከኢህአዴግም እንኮርጃለን፡፡ ኩረጃ መጥፎ የሚሆነው ትምህርት ቤት ነው፡፡›› የሚለው ደግሞ ለሁለተኛው ጥያቄ የሰጡት ምላሽ ነው፡፡›› ነገሩ አሁን ነው የመጣው፡፡ በሁለት ንዑሳን ርዕሶች በማጀብ ‹‹ፓርላማው የኑሮ ውድነት immunity አለው እንዴ? በሚል ርዕስ ኤሊያስ የተባሉት ቋሚ የአዲስ አድማስ አምደኛ በዚሁ በየካቲት 3 ቀን 2004 ዓ.ም እትም ላይ ጽፈዋል፡፡ ሰሞኑን ጠቅላይ ሚኒስትሩ ያቀረቡትን የስድስት ወራት የመንግሥት ሥራ አፈጻጸም ሪፖርት እና የፓርላማውን ውይይት መሠረት በማድረግ የተጻፈው የኤሊያስ ሰ ጽሁፍ ላይ አሁን አንድ ነገር አየሁ፡፡ ‹‹የአመራር ፓርቲ ተወካዮች በፖለቲካው ኮሚኒው ውስጥ የተሰጣቸው ሚና ፓርላማውን በሳቅ ማጀብ ብቻ ነው እያልኳችሁ ነው፡፡ እኔን ካላመናችሁኝ ብቸኛው የተቃዋሚ ፓርቲ ተወካይ የሆኑት የተከበሩ አቶ ግርማ ስለፓርላማው ሳቅ ተጠይቀው የመለሱትን እንደማስረጃ አቀርባለሁ›› ይሉና ‹‹ጠቅላይ ሚኒስትሩ በየስድስት ወሩ አንዴ እየመጡ ቢያስቋቸው ምንም ክፋት የለውም፤ የተመረጡት ለማሳቅ ከሆነ…እንደምታዩኝ እኔ ቂጭ ብዬ የተመረጥኩበትን ዓላማ ሰርቼ ነው የምወጣው›› የሚል ማስረጃቸውን ጸሀፊው አቀረቡ፡፡ ለመሆኑ የተከበሩ አቶ ግርማ ይህን ያሉት እርስዎ አቶ ግርማ ብለዋል ባሉበት ቀን በወጣ የአዲስ አድማስ እትም ላይ መሆኑን የማናውቅ መስሎት ይሆን? ወይስ በአንድ ጋዜጣ ላይ በተመሳሳይ ቀን በወጣ ህትመት ላይ አንዳችሁ ለአንዳችሁ ማስረጃ ሆናችሁ የቀረባችሁት መንገድ ከምን የመጣ ይመስሎታል? በዚህ ብቻ ቢያበቁ ጥሩ፡፡ ስለ ኩረጃ የተከበሩ አቶ ግርማ የተናገሩትን እና በዚያው ጋዜጣ ላይ ያየነውን እርስዎ ከሰሞኑ አቶ ግርማ በአንድ ጋዜጣ ላይ እንደተናገሩት ብለው ቃል በቃል መጻፍዎስ? ምንጩ ምን ይሆን? አቶ ግርማ ያሉት የኩረጃ አሪፍነት እኮ እንዲህ ዓይነቱን አይደለም፡፡ ይኼ ማታለል፤ በአንባቢ ላይ መዘባበት ነው፡፡ ለነገሩ እናንተ የአንድ ሣንቲም ገጽታዎች ስለመሆናችሁ እኛ እንደምናውቅ እርስዎም የተረዱ ይመስለኛል፡፡ በጽሁፍዎ መግቢያ አካባቢ ለተቃዋሚና ገዢው ፓርቲ ምክር ቢጤ ጣል አድርገው ሳይጠየቁ በቅንፍ ‹‹እኔ ከሁለቱም ጎራ አይደለሁም›› ሲሉ ነው እራሱን ያላመነ እንዲሉ የነቃሁብዎት፡፡ እናንተ

ማለት እንግዲህ እንዲህ ናችሁ፡፡ ሲሻችሁ ተቃዋሚ ፓርቲ ሲያሻችሁ ጋዜጠኛ/አምደኛ፡፡ ይህ መሆኑ ለኔ አልገረመኝም፡፡ እንዲህ ዓይነት ስህተት በምንም ምክንያት በአጋጣሚ እንደማይፈጠር ይታወቃል፡፡ ሆኖም ይህን ኦዲት ለማድረግ ጋዜጠኛ መሆን አይጠይቅም፡፡ የትኛውም አንባቢ በግልጽ አይቶ እንደ አንባቢ ማረም ይቻለዋል፡፡ የአድማስ ኤዲቶሪያል ቀደም ብዬ እንደጠቀስኩት በዜሮ ድምር ፖለቲካ ከእነዚህ ኃይሎች ጋር የተጋመደ በመሆኑ አይቶ እንዳላየ ዘሎታል፡፡ ይሄ ተቃውሞ አይደለም፤ አንባቢን መናቅ ነው፡፡ ደንበኛን ማሸሽ ነው፡፡

ኤሊያስ ሰ አቶ ግርማ ሰይፉ የተከበሩ የተባሉት በፓርላማው መሆኑንና የሕዝብ ውክልና ስላላቸው መሆኑን በመዘንጋትና እሳቸው በግል የሰጧቸው ክብር የሆነ መስሏቸው የተከበሩ ሲሉ አቶ ግርማ የሰጡትን የምክር ቤት ሞገስ ለመላው የፓርላማ አባል ይነፍጋሉ፡፡ ነፍገው ብቻ አያበቁም፤ ይዘልፋሉም፡፡ ኤሊያስ ሰ እራስዎ በራስዎ ጊዜ ማንነትዎን አጋልጠዋል፡፡ አላዛር ኬሞ በሰራው ፋይል መጋለጡ አስደንብሮት ጠፍቷል፡፡ እርስዎ እንዳይጠፉ አደራ፡፡ እንዲህ እያደረጉ ማንነታችሁን ይንገሩን፡፡ የዴሞክራሲያችንና የልማታችን ፀር የሆነውን ክፍል ብናውቅ ይጠቅመናል፡፡ የፍልሚያን አቅጣጫ እንለይበታለን፡፡

ስለህገ መንግሥቱ በመሰላቸው ቀን ወዳጅ መስለው የሚዘምሩት የተከበሩት አቶ ግርማ ሰይፉ እንደ አስፈላጊነቱ ህገ መንግሥቱን እንደሚጠቀሙ እንጂ ለህገ መንግሥቱ ከበሬታ የሌላቸው እንደሆነ በጠቅላይ ሚኒስትሩ በተጋለጡበት ማግስት እርስዎ ደግሞ አላዋቂ ሰሚ ሆነው አጋልጠው ሰጧቸው፡፡

የተከበሩት ፀሃፊና የምክር ቤት አባል እናንተ በፓርላማ ያላችሁ ወንበር አንድ በመቶም ሆነ 41 በመቶ ለእኛ ሳይሆን በፖለቲካ ሳይንስ መርሆም ልዩነት የለውም፡፡ በርግጥ ከመከራከርና በፓርላማ ብዙ ሰዓት ከማግኘት አኳያ ሊጠቅማችሁ ይችል ይሆናል፡፡ ለእኛ እንደዜጋ የሚጠቅመን አጠቃላዩ የመድብለ ፓርቲ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታውን የተመለከተው ነው፡፡ የእኛ የፓርላማ ክርክር ሁለት በማይገናኙ የፖለቲካ ኃይሎች መካከል የሚደረግ ነው፡፡ ቢያንስ የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ የህጎች ሁሉ የበላይ የሆነውን ህገ መንግሥት ከመቀበል ይጀምራል፡፡ ይህ ባልሆነበት ሁኔታ የተቃዋሚው ወንበር አንድ በመቶ ሆነ 40 በመቶ ለልማታችንም ሆነ ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት

ግንባታችን ፋይዳ የለውም፡፡ መንገዳችሁ ሁሉ እንደሚንሸዋሸው ፀናድል ነው፡፡ ይብላኝላችሁ፡፡